# አትወለድ ይቅር !

( አሥራደው ከፈረንሳይ )



አትወለድ በበረት - ዕበት አይሸተትህ፤
ሳር ቅጠል ጎዝጉዘህ - ይቅር መተኛትህ
ድንጋዩ አይቆርቁርህ -መደቡ አይጎርብጥህ
የከብቶች እስትንፋስ - አትሙቅ ይቅረብህ፤
መከራዋ አይብዛ - አትቸገር ማርያም፤
የዎሴፍም ይረፍ - በበረሃ አይድከም ፤
የለመድነው ስቃይ - መከራችን ላይቀር፤
ክርስቶስ አትምጣ - አትወለድ ይቅር ።

እኛ እንደሁ አንማር - በደል ተስማምቶናል፤
ነፃነት ተረስቶን ባርነት ለምደናል ።

በዕምነት፤_ ተራቁተን !
በሥጋ፤_ በስብሰን !
በመንፈስ፤_ ደህይተን !
በቁማችን ሞተን - ክርፋት፤_ ክርፋት ስንሸት፤
ምናችን ሊለወጥ_?! ምናችን ሊቀየር_?! በክርስቶስ ውልደት ።

አንማርም እኛ - ማሰብ ተስኖናል፤
በደል ጥቃት ለምደን - ባሪያዎች ሆነናል።

አምላክም አታስብ፤
አትቸገር ይቅር !
ልጅህን አትላክ - ለስቃይ ወደ ምድር፤
ለምን_? ተፀንሶ - ለምን_? ይወለዳል !
ለምን_? በበረት ውስጥ መከራውን ያያል ።

ኮት፤ ሸሚዛችሁን - ዳግም ገልብጡና፤
ለፓርቲ መጠርያ - ሌላ ስም አውጡና፤
ተስማምታችሁ ግዙን! - አንድላይ ሁኑና፤
እያልን በተማጽኖ፤ ገብተናል ልመና ።

እኛ እንደሁ አንማር ጭራሽ ደንቁረናል፤
እነዛኑ ገዳዮች፤_ አሳሪ ገራፊ_፤ ኑ! ግዙን ብለናል።

ያሰብንበት ሳንደርስ :
ገና ብዙ ርቀት - ቀርቶን እያያችሁ፤
ቀናቱን፤ ሳምንቱን፤ - ወራቱን ቆጥራችሁ፤
እንኳን አደረሰህ !
እናንተም አትበሉኝ - እኔም አልላችሁ ።

ክርስቶስ አትምጣ - አትወለድ ይቅር፤
ሃሞት ለሌለው ሰው ብዙም አትቸገር ።

እኛ እንደሁ አንማር - በደል ተስማምቶናል፤
ነፃነት ተረስቶን ባርነት ለምደናል ።

ህይወት ተጠይፋ - መከራ እጮኛ አርጎን ፤
የሞት ሞት ሠርጎ - ሙሽራ አርጎ ድሮን፤
እንደ ሚስት፤ እንደ ባል፤ - ጥላቻን አግብተን፤
የተማርነው ትምርት - ደግሞ ደግሞ መግደል፤_ ድግግም ሞት መሞት፤
ታዲያ!
ምናችን ሊለወጥ_?! ምናችን ሊቀየር_?! በክርስቶስ ውልደት ።

አንማርም ከቶ - እኛ ደንቁረናል፤
በደል ጥቃት ለምደን ባሪያዎች ሆነናል።

ለአምላኬ ስሞታ፤ ለህዝቤ ወቀሳ፤ ለአገሬ ፍቅር፤ ለራሴ ቁጭት፤ ለወጣቱ ትምህርት፤ ተብላ የተቋጠረች

ተጣፈ ታኅሣሥ 2 ቀን 2012 ዓ.ም. በነጮች ( 12/12/2019